# ዘጠና አምስቱ

# የሉተር

# መከራከሪያ

# ነጥቦች



# ዘጠና አምስቱ
# የሉተር መከራከሪያ ነጥቦች ።

በአማርኛ ያዘጋጀው ፡- ደረሰ ብሩ ።

መካነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል ።

አዲስ አበባ 1988 ዓ. ም.

Scanned by CamScanner

# የእግዚአብሔር ቃል ።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ፥ «ኃጢአትህ እንደ ተሰረየልህ ይሰማሃልን ?» ሲል ሉተርን ጠየቀው ። ሉተር እንዲህ ሲል መለሰለት ፥ «አይሰማኝም ፥ ነገር ግን ኃጢአቴ እንደተሰረየልኝ በሰማይ እግዚአብሔር የመኖሩን ያህል እርግጠኛ ነኝ ። ምክንያቱም ስሜት ይመጣል ፥ ስሜት ይሄዳል ። ስሜት አታላይ ነው ። ሊታመን የሚገባው ሌላ ነገር የለም ።

«ምንም እንኳ ልቤ የሚያጓጓውን ስጦታ ስለ አጣ የሕሊና ወቀሳ የደረሰበት መስሎ ቢሰማውም ፥ ቃሉ ሊሻር የማይችል ከልቤ የሚበልጥ ኣለ ። ነፍስና ሥጋዬ እስኪለያዩ ድረስ በማይለዋወጠው ፍቅሩ አምናለሁ ። ሌላው ነገር ሁሉ የሚያልፍ ቢሆንም እንኳ ቃሉ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ።»

ማርቲን ሉተር እ ኣ.ኣ. 1483—1546



Scanned by CamScanner

# ማርቲን ሉተር ።

እ.አ.አ. ኅዳር 10 ቀን 1483 ዓ.ም. በሳክሶኒ ጀርመን በምትገኝ አይስሌበን በተባለች መንደር የተወለደውና የካቲት 18 ቀን 1546 ዓ.ም. በ63 ዓመቱ ያረፈው ማርቲን ሉተር በዘመኑ በአውሮጳ የተቀጣጠለው የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሪ ነበር ። አባቱ ሐንስና እናቱ ማርጋሬት ዚግለር ሉተር ድሆች ገበሬዎች ስለ ነበሩ ከችግሩ የተነሣ እየለመነ ትምህርቱን የተማረበት ጊዜ ነበረ ። በትምህርቱ ጉብዝናን ስለ አሳየ በነበረበት ዩኒቨርስቲ እጅግ በጣም ታዋቂነትን ከአተረፉ ተማሪዎች አንዱ ለመሆን በቅቶ ነበር ።

አንድ ቀን በኤርፉርት አቅራቢያ ኃይለኛ መብረቅ ወረደና የሞት ፍርሃት አሳደረበት ። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ወደ አጉስቲኒያን ገዳም ገብቶ የምንኵስና ኑሮውን ተያያዘው ።

እ.አ.አ. በ1510 ዓ.ም. ለሥራ ጉዳይ ወደ ሮማ ሄዶ እያለ በቤተ ክርስቲያን ይታይ በነበረው አስተዳደራዊና ሥነ ምግባራዊ ጉድለት ልቡ አዘነ ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሊቀ ጳጳሳት ሌዎ አሥረኛ የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን አሳድሶ ለማሠራት አንድ ዘዴ አቅዶ በሥራ ላይ አዋለ ። ይኸውም ገንዘብ ለሚሰጡ ሰዎች የኃጢአት ይቅርታ ተስፋ

የሚሰጥ የስርየት ጽሑፍ በይፋ እንዲሸጥ አዘዘ ። ይህ ድርጊቱ ሉተርን ለተቃውሞ አነሣሣው ። ከዚያ በፊት በጥልቀት ያነበበውና ያጠናው የእግዚአብሔር ቃል በተለይም በሮሜ 1፥17 የሚገኘው «ጻድቅ በእምነት ይኖራል» የሚለው ቃል ሕይወቱን ስለ ለወጠው ፣ የሊቀ ጳጳሳት ሌዎን ስሕተት አይቶ በቸልታ ሊያልፈው አልቻለም ።

በዚህ ምክንያት እ.አ.አ. በ1517 ዓ.ም. ዘጠና አምስት መከራከሪያ ነጥቦችን በዊንትንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ በመዶሻ ጠረቀ ። ዘጠና አምስቱ መከራከሪያ ነጥቦች ሊቀ ጳጳሳቱ በስርየት ጽሑፍ አማካይነት የኃጢአት ይቅርታ ለማስጠት ያደርገው የነበረውን ሙከራ የሚቃወሙ ነበሩ ። ሉተር በእነ ዚህ ነጥቦች አማካይነት ፣ ጽድቅ የሚገኘው በሌላ በማንኛውም መንገድ ሳይሆን በእምነት መሆኑን አረጋገጠ ። ሐሳቡን እንዲለውጥ ቢነገረውም ከመ ጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ ካልተሰጠው በቀር ከተነ ሣበት ዓላማ ንቅንቅ እንደማይልና እምነቱን እንደ ማይተው አጽንቶ ተናገረ ።

ብዙ ክስ ፣ ብዙ ውጣ ውረድና እንግልት ቢደ ርስበትም ከጊዜ በኋላ ሉተር በመጽሐፍ ቅዱስ እው ነት ላይ ተመሥርቶ ያቀረበው ሐሳብ ተቀባይነትን በማግኘቱ ፣ ብዙ ተከታዮችን ሊያፈራ ቻለ ።

ምኞቱና ፍላጎቱ ፣ ጥረቱም በሮማ ቤተ ክርስ ቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ተሐድሶ እንዲኖር ለማድረግ



Scanned by CamScanner

እንጂ ለመገንጠል አልነበረም ። ከፍላጎቱ ውጪ በሆነ ምክንያት ይህ ሐሳቡ ከግቡ ባይደርስም ፤ በእርሱ መሣሪያነት እግዚአብሔር ብዙዎችን ከጨለማ ወደ ወንጌል ብርሃን ሊያወጣ በመቻሉ ድካሙ ከንቱ ሆኖ አልቀረም ።

ማርቲን ሉተር ለዘመናት ተዳፍኖ ለነበረው የወንጌል እሳት መቀጣጠልና ለቤተክርስቲያን ተሐድሶ አራማጆች ቁጥር መጨመር ፤ ደግሞም ለፕሮቴስታንት እምነት መመሥረት ምክንያት በመሆኑ ፤ ስሙ በታሪክ ማኅደር ውስጥ ጉልህ የሆነ ስፍራ ይዞ ይገኛል ።

ከዚህ ቀጥሎ ለሉተር በሮማ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ላይ መነሣት ምክንያት የሆኑትን ዘጠና አምስት መከራከሪያ ነጥቦች እንመለከታለን ።

## ዘጠና አምስቱ የሉተር መከራከሪያ ነጥቦች ።

1. ጌታችንና መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ «ንስሐ ግቡ» (ማቴ 4፥17) ባለ ጊዜ ፤ የአማኞች ሕይወት በአጠቃላይ የንስሐ ሕይወት እንዲሆን አዘዘ ።
2. ይህ ቃል በቀሳውስት አናዛዥነት የሚከናወነውን ምሥጢረ ንስሐ ፤ ይኸውም ኑዛዜና



Scanned by CamScanner

በእርሱም ምክንያት የሚገኘውን ደስታ እን ደሚያመለክት ተደርጎ ሊታይ አይችልም ።

3. ይሁን እንጂ ቃሉ ውስጣዊ ንስሐ ማለት ብቻም አይደለም ፤ ይህን የመሰለው ውስጣዊ ንስሐ ውጫዊ የሆነ የተለያየ ዓይነት ሥጋዊ መሞትን ካላስከተለ በቀር ዋጋ የለውም ።

4. በኃጢአት ላይ የሚሰጥ ቅጣት ራሳችንን ጠልተን ፥ ይኸውም እውነተኛ የሆነ ውስጣዊ ንስሐ ገብተን ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት እስ ክንገባ ድረስ ይቆያል ።

5. ሊቀ ጳጳሳቱ በገዛ ሥልጣኑ ወይም በቀኖና (በንስሐ ሕግጋት) ከተደነገገው ቅጣት በቀር ማንኛውንም ቅጣት የመማር ምኞትም ሆነ ችሎታ የለውም ።

6. ሊቀ ጳጳሳቱ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ከማሳ የትና ከማወጅ በቀር ፥ በእርሱ ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ከተደነገጉ ነገሮች ሌላ ምንም ዓይ ነት በደል ለማስወገድ አይችልም ። ይቅርታ ሊሰጥ የተደነገጉ ነገሮች ቸል ከተባሉ ግን ይቅርታ አይኖርም ።

7. እግዚአብሔር ፥ በሁሉም ነገር ዝቅ እንዲልና ለገዚዙ ማለትም ለቄሱ እንዲታዘዝ ካላደረገው በቀር የማንንም በደል አይምርም ።

8. ንስሐን የሚመለከተው ቀኖና የተደነገገው በሕያዋን ላይ ብቻ ነው ፣ በሕጉ መሠረትም በሙታን ላይ ምንም ነገር መደንገግ አይገባም ።

9. ስለዚህ ሊቀ ጳጳሳቱ በሚያወጣው ድንጋጌ ሞትን የሚመለከተውንና አስፈላጊ ሆኖ የሚያገኘውን ክፍል (አንቀጽ) ዘወትር ለየት አድርጎ የሚያየው እስከ ሆነ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ አማካይነት ለእኛ ቸርነትን ያሳየናል ።

10. በቀኖና ውስጥ የተመለከቱትን ቅጣቶች ለዓፀደ ንስሐ ጊዜ የሚያቆዩ ቀሳውስት የድንቁርናና የክፋት ድርጊት ይፈጽማሉ ።

11. በቀኖና ውስጥ የተጠቀሰውን ቅጣት በዓፀደ ንስሐ ወደሚፈጸም ቅጣት የሚለውጡት እነዚያ እንክርዳዶች የተዘሩት ያለጥርጥር ጳጳሳት ተኝተው ሳሉ ነው (ማቴ. 13 ፥ 25) ።

12. በድሮ ዘመን በቀኖና የተደነገጉ ቅጣቶች በሰው ላይ የሚጣሉት ከፍታት በኋላ ሳይሆን በፊት ነበር ።

13. ሙታን በሞት አማካይነት ከቅጣት ሁሉ ነጻ ይወጣሉ ። ቀኖናን በሚመለከት ቀድሞውኑ የሞቱ ናቸው ። በመሆኑም ከቅጣት የመፈታት መብት አላቸው ።



Scanned by CamScanner

14. ሟቹ ሰው መንፈሳዊነት ወይም ፍቅር የሚጐድለው ከሆነ ፤ ይህ ነገር ታላቅ ፍርሃት ያስከትልበታል ፤ ፍቅሩ ባነሰ መጠን ፍርሃቱ እየጨመረ ይሄዳል ።

15. ይህ ፍርሃት ወይም ድንጋጤ ራሱ ሌሎችን ነገሮች ሳንጨምር የዐፀደ ንስሐ ቅጣት ለመሆን የሚችል ነው ። (ምክንያቱም ወደ ተስፋ መቁረጥ ድንጋጤ የሚጠጋ ነውና ።)

16. በሲኦል ፤ በዓፀደ ንስሐና በሰማይ መካከል ያለው ልዩነት በተስፋ መቁረጥ ፤ በፍርሃትና በደኅንነት መካከል ያለውን ልዩነት ይመስላል ።

17. በዓፀደ ንስሐ ያሉት ነፍሳት ፍርሃት የሚቀንስላቸው ፤ ፍቅር ግን የሚበዛላቸው ይመስላል ።

18. ከዚህም በላይ በአእምሮ ሆነ በእግዚአብሔር ቃል በዓፀደ ንስሐ ያሉ ነፍሳት ከበጎ ምግባር ውጪ ናቸው ፤ ወይም በፍቅር ሊያድጉ አይችሉም የሚያሰኝ ነገር የለም ።

19. ወይም ደግሞ እኛ ራሳችን ስለ ደኅንነት ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ብንሆንም እንኳ ፤ በዓፀደ ንስሐ ያሉ ፤ ቢያንስ የተወሰኑ ነፍሳት ፤ እርግጠኞች የመሆናቸውና የገዛ መዳናቸውንም የማወቃቸው ነገር አልተረጋገጠም ።

20. ስለዚህ ሊቀ ጳጳሳቱ ፤ «ለቅጣት ሁሉ ሙሉ



Scanned by CamScanner

ምሕረት» የሚሉትን ቃላት በሚጠቀምበት ጊዜ ራሱ በሰዎች ላይ የጣለውን እንጂ ፤ በእውነቱ «ቅጣት ሁሉ» ማለት አይደለም ።

21. በመሆኑም ሰው ከበደል ሁሉ ነጽቶ በሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ ይድናል የሚሉ የስርየት ጽሑፍ ሰባክያን የተሳሳቱ ናቸው ።

22. እንደ እውነቱ ከሆነ ሊቀ ጳጳሳቱ በዓፀደ ንስሐ ያሉ ነፍሳት በቀኖና መሠረት በሕይወቱ ሥጋ እያሉ መቀበል ለነበረባቸው ቅጣት ምሕረት እንዲያገኙ ማድረግ አይችልም ።

23. የትኛውንም ዓይነት ቅጣት ሁሉ በሚመለከት ለማንኛውም ሰው ምሕረት ማድረግ የሚቻል ከሆነ ፣ እጅግ በጣም ፍጹማን የሆኑትን ይኸውም ጥቂቶችን ብቻ ነው መማር የሚቻለው ።

24. በዚህ ምክንያት ከቅጣት ነጻ መውጣትን በሚመለከት ልዩነት በማያደርገውና ታላቅ በሆነው ተስፋ ብዙ ሰዎች የተታለሉ ናቸው ማለት ነው ።

25. ሊቀ ጳጳሳቱ በአጠቃላይ በዓፀደ ንስሐ ላይ ያለው ሥልጣን ማንኛውም ጳጳስ ወይም መምህር በተለየ መንገድ በራሱ ሀገረ ስብከት ላይ ካለው ሥልጣን ጋር የሚመሳሰል ነው ።

26. ሊቀ ጳጳሳቱ በዓፀደ ንስሐ ውስጥ ያሉ ነፍሳትን



Scanned by CamScanner

በሚመለከት ለራሱ በሌለው ቁልፍ ኃይል ሳይሆን ስለ እነርሱ በሚያደርገው ምልጃ ለመማር ማሰቡ የተሻለ ነው ።

27. ሳንቲሙ በገንዘብ ሳጥን ውስጥ ቅጭል ሲል ነፍስ ከዓፀደ ንስሐ ብር ብላ ትወጣለች የሚሉ ፣ የሰውን ትምህርት ብቻ የሚያስተምሩ ናቸው ።

28. ሳንቲም በገንዘብ ሳጥን ውስጥ ቅጭል ሲል ስስትና ንፉግነት ሊጨምር እንደሚችል የተረጋገጠ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ስታማልድ ግን ውጤቱን ከእግዚአብሔር መጠበቅ ይቻላል ።

29. ስለ ቅዱስ ሴቬሪኑስና ቅዱስ ፓስካል በተነገረው አፈ ታሪክ ውስጥ እንደምናገኘው ያልተለመደ ሁኔታ ፣ በዓፀደ ንስሐ ያሉ ነፍሳት ሁሉ ለመዳን ይመኙ እንደ ሆነ ማን ያውቃል ።

30. ማንኛውም ሰው ሙሉ የሆነ የኃጢአት ስርየት ማግኘቱ ቀርቶ ስለ ራሱ ጸጸት ፍጹምነት እርግጠኛ አይደለም ።

31. የስርየት ጽሑፍ የሚገዛ ሰው በእውነት እንደሚጸጸት ሰው ሁሉ የማይገኝ ነው ፣ በእርግጥም ከልክ ያለፈ ልዩ ነው ።

32. የስርየት ጽሑፍ ስላላቸው በመዳናቸው እርግጠኝነት የሚያምኑ ሰዎች ከነአስተማሪዎቻ



Scanned by CamScanner

ቻው ጭምር ለዘላለም ይኮነናሉ ።

33. ሰዎች ፣ በተለይ ሊቀ ጳጳሳቱ የሚያደርገው ይቅርታ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅ በት ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ከሚሉ ክፍሎች መጠንቀቅ አለባቸው ።

34. በስርየት ጽሑፍ የሚገኝ ጸጋ ሰው ካቋቋመው ከጸጋ ምሥጢራት ጋር በተያያዘ መልኩ ያለ ውን ቅጣት ብቻ የሚመለከት ነውና ።

35. ከዓፀደ ንስሐ ውስጥ ነፍሳትን ገዝቶ ለማውጣት ወይም ንስሐ የሚያስገኘውን ልዩ መብት ለመግዛት በሚፈልጉት ሰዎች ረገድ ጸጸት አስፈላጊ አይደለም ብለው የሚያስተምሩ ሰዎች ክርስቲያናዊ ያልሆነ ትምህርት ያስተምራሉ ።

36. በእውነት ንስሐ የሚገባ ክርስቲያን የስርየት ጽሑፍ ባይኖረውም እንኳ የሚደርስበትን ቅጣ ትና የፈጸመውን በደል በሚመለከት ሙሉ ምሕረት የማግኘት መብት አለው ።

37. በሕይወት ሥጋ ያለም ሆነ የሌለ ማንኛውም እውነተኛ ክርስቲያን የክርስቶስንና የቤተክር ስቲያንን በረከት ሁሉ ይካፈላል ። ይህ የስ ርየት ጽሑፍ ባይኖረውም እንኳ እግዚአብ ሔር ይሰጠዋል ።

38. ይሁን እንጂ ሊቀ ጳጳሳቱ የሚሰጠው የኃጢ



Scanned by CamScanner

አት ስርየትና ቡራኬ በምንም ዓይነት በቸልታ ሊታይ አይገባም ፤ ቀደም ሲል እንዳልሁት (መከራከሪያ ነጥብ 6) የመለኮታዊው ምሕረት አዋጅ ነውና ።

39. የስርየት ጽሑፍን ጥቅምና የእውነተኛ ጸጸትን አስፈላጊነት በአንድ ጊዜ ለሕዝቡ ማስተማር እጅግ በጣም ለተማሩ የሥነ መለኮት አዋቂ ዎች እንኳ በጣም አስቸጋሪ ነው ።

40. በእውነት የሚጸጸት ክርስቲያን የኃጢአቱን ቅጣት መቀበል ይፈልጋል ፤ ይሁን እንጂ የስ ርየት ጽሑፍ መትረፍረፍ ቅጣትን ያቃልላል ፤ ሰዎች እንዲጠሉትም ያደርጋል ።

41. ሰዎች በስሕተት ከሌላ ዓይነት በጎ የፍቅር ሥራ የተሻለ ነው ብለው እንዳያስቡ የሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ በጥንቃቄ መሰበክ አለበት ።

42. ሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ ግዥ በምንም ዓይነት ከፍቅር ጋር መነጻጸር አለበት ብሎ እን ደማያስብ ክርስቲያኖች መማር ይኖርባቸዋል ።

43. ለድሀ የሚሰጥ ወይም ለችግረኛ የሚያበድር ፤ የስርየት ጽሑፍ ከሚገዛ ሰው ይልቅ መልካምን ሥራ እንደሚያደርግ ፤ ክርስቲያኖች መማር ይኖርባቸዋል ።



Scanned by CamScanner

44. ፍቅር የሚያድገው በፍቅር ሥራ ቢሆን ፣ ሰው የተሻለ ይሆናል ። ይሁን እንጂ ሰው የተ ሻለ የሚሆነው በስርየት ጽሑፍ አማካይነት አይደለም ። ነገር ግን ከቅጣት ብቻ ነጻ ይሆናል ።

45. የተቸገረን ሰው አይቶ የሚያልፈው ፣ ገንዘቡን ግን ለስርየት ጽሑፍ የሚሰጥ ፣ የሊቀ ጳጳሳቱን የስርየት ጽሑፍ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቍጣ መግዛቱ እንደሆነ ክርስቲያኖች መማር ይኖር ባቸዋል ። ።

46. ክርስቲያኖች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ከሌላ ቸው ቢቀር የቤተ ሰባቸውን ፍላጎት ለማሟላት ማስቀመጥ እንጂ በምንም ዓይነት ለስርየት ጽሑፍ ሲሉ ገንዘብ ማባከን እንደሌለባቸው መማር ይኖርባቸዋል ።

47. የስርየት ጽሑፍ ግዥ ትእዛዝ ሳይሆን የነጻ ምርጫ ጉዳይ መሆኑን ክርስቲያኖች መማር ይገባቸዋል።

48. ሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ ለሰዎች ሲሰጥ ፣ ከገንዘባቸው ይልቅ በታማኝነት የሚጸልዩት ጸሎት እንደሚያስፈልገው ክርስቲያኖች መ ማር ይገባቸዋል ።

49. የሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ የሚጠቅመው እምነታቸውን በእርሱ ላይ እስካላደረጉ ድረስ



Scanned by CamScanner

ብቻ እንደሆነ ፣ በእርሱ ምክንያት እግዚአብ ሔርን መፍራታቸውን ከተው ግን በጣም ጎጂ መሆኑን ክርስቲያኖች መማር ይገባቸዋል

50. ሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ ሰባክያን ሰውን እያስገደዱ ገንዘብ እንደሚያስከፍሉ ቢያውቅ ኖሮ ፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን በበጎቹ ቆዳ ፣ ሥጋና ዓፅም ከሚታነጽ ይልቅ ተቃጥሎ ወደ አመድነት ቢለወጥ የሚሻል መሆኑን ክርስቲያኖች መማር ይገባቸዋል ።

51. ሊቀ ጳጳሳቱ የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን መሸጥ ቢኖርበትም እንኳ ፣ አንዳንድ የስርየት ጽሑፍ ነጋዴዎች እያታለሉ ገንዘብ ለሚወስ ዱባቸው ለብዙዎች የራሱን ገንዘብ ለመስጠት መሻት እንደሚኖርበት ፣ እንደሚገባውም ክር ስቲያኖች ሊማሩ ይገባል ።

52. የስርየት ጽሑፍን በሚመለከት የሊቀ ጳጳሳቱ እንደራሴ የሆነው ሰው ፣ ሊቀ ጳጳሳቱም ሳይ ቀር በዋስትናነት ነፍሱን የሚሰጥ ቢሆን እንኳ ፣ በስርየት ጽሑፍ አማካይነት ደኅንነትን ለማግ ኘት መተማመን ከንቱ ነው ።

53. በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የስርየት ጽሑፍ ይሰበክ ዘንድ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያ ናት የእግዚአብሔር ቃል ጨርሶ እንዳይሰበክ



Scanned by CamScanner

የሚከለክሉ ፥ የክርስቶስና የሊቀ ጳጳሳቱ ጠላቶች ናቸው ።

54. በአንድ ስብከት ውስጥ ፥ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ለስርየት ጽሑፍ እኩል ወይም በዛ ያለ ጊዜ ከተሰጠ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በደል መፈጸም ነው ።

55. እጅግ ኢምንት የሆነው የስርየት ጽሑፍ በአንድ የደወል ድምፅ ፥ በአንድ ዑደት ፥ እንዲሁም በአንድ ሥነ ሥርዓት የሚከበር ከሆነ ፥ ከሁሉ የሚበልጠው ወንጌልማ በመቶ የደወል ድምፅ ፥ በመቶ ዑደት ፥ በመቶ ሥነ ሥርዓት መከበር እንዳለበት በእርግጥ የሊቀ ጳጳሳቱ ስሜት ነው ።

56. ሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ በማውጣት የሚያሠራጭበት የቤተ ክርስቲያን መዛግብት ላይ ክርስቲያኖች በሚገባ አልተወያዩባቸውም ወይም አያውቋቸውም ።

57. የስርየት ጽሑፍ ምድራዊ መዝገብ አለመሆኑ በእርግጥ ግልጽ ነው ፥ ምክንያቱም ብዙ ሰባክያን ይሰበስቡታል እንጂ በነጻ አያድሉትም ።

58. የስርየት ጽሑፍ የክርስቶስና የቅዱሳን በጎ ምግባርም አይደለም ፥ ያለ ሊቀ ጳጳሳቱ እንኳ ቢሆን ክርስቶስና ቅዱሳን ለመንፈሳዊ ሰው



Scanned by CamScanner

ጸጋን ፣ ለአዳማዊ ሰው መስቀልን ፣ ሞትንና ሲኦልን ዘወትር ይሠራሉ ።

59. ቅዱስ ሎሬንስ የቤተ ክርስቲያን ድሆች የቤተ ክርስቲያን ሀብት ናቸው ብሎ ነበር ፣ ይሁን እንጂ እርሱ ይህን የተናገረው በዘመኑ ይጠቀሙበት በነበረው የቃሉ አገባብ መሠረት ነው ።

60. በነገሩ ማሰብ ምንም ሳያስፈልግ ክርስቶስ በፈጸመው በጎ ምግባር ምክንያት የተሰጡት የቤተ ክርስቲያን ቁልፎች ያ መዝገብ ናቸው እንላለን ።

61. ቅጣትንና እርሱን የሚመለከቱትን ጉዳዮች ለመማር ፣ የሊቀ ጳጳሳቱ ሥልጣን በራሱ በቂ እንደሆነ ግልጽ ነው ።

62. እውነተኛው የቤተ ክርስቲያን መዝገብ እጅግ በጣም ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር ክብርና ጸጋ ነው ።

63. ይህ መዝገብ ግን በተፈጥሮው እጅግ የተጠላ ነው ፣ ምክንያቱም ፊተኞችን ኋላኞች ያደርጋል ማቴ. 20 ፣ 16 ።

64. በሌላ በኩል የስርየት ጽሑፍ መዝገብ የኋለኞችን ፊተኞች ስለሚያደርግ እጅግ በጣም ተቀባይነት ያለው ነው ።



Scanned by CamScanner

65. ስለዚህ የወንጌል መዝገብ ቀደም ሲል እንዱ ባለጠጎችን ያጠመደበት መረብ ነው ።

66. የስርየት ጽሑፍ መዝገብ በአሁኑ ጊዜ አንዱ የሰዎችን ሀብት የሚያጠምድበት መረብ ነው ።

67. ቀስቃሾች ከሁሉም የላቀ የጸጋ ናቸው የሚሉአቸው የስርየት ጽሑፎች ይህንን ትርጉም ያገኙት ከጥቅም አንጻር ነው ።

68. እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከእግዚአብሔር ጸጋና ከመስቀሉ ቅድስና ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ኢምንት የሆነ ጸጋ ነው ።

69. ጳጳሳትና ቀሳውስት የሊቀ ጳጳሳቱን የስርየት ጽሑፍ በሚመለከት የእርሱ እንደራሴዎች የሆኑ ሰዎችን ሲታላቅ አክብሮት መቀበል አለባቸው ።

70. ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች ሊቀ ጳጳሳቱ ባዘዘው ነገር ፈንታ የራሳቸውን ሐሳብ እንዳይሰብኩ ዓይኖቻቸውንና ጆሮዎቻቸውን ይበልጥ ማድከም አለባቸው ።

71. የሊቀ ጳጳሳቱን የስርየት ጽሑፍ በሚመለከት ሐሰትን የሚናገር ሰው የተወገዘና የተረገመ ይሁን ።

72. ከስርየት ጽሑፍ ሰባክያን ምኞትና ፈቃድ ራሱን የሚጠብቅ ሰው ግን ቡሩክ ይሁን ።



Scanned by CamScanner

73. ሊቀ ጳጳሳቱ በማንኛውም ረገድ የስርየት ጽሑፍ ሽያጭን በሚመለከት ፣ በደል በሚ ፈጸሙ ሰዎች ላይ የማስፈራሪያ ጩኸት ማሰ ማቱ የማይቀር ነው ።

74. በተቀደሰ ፍቅርና እውነት ላይ በደል ለመፈ ጸም ሲሉ የስርየት ጽሑፍን ለመጠቀም ሰበብ በሚፈልጉ ሰዎች ላይ የሚበልጥ የማስፈራ ሪያ ጩኸት ያሰማል ።

75. የማይገባ ነገር ያደረገና እመ አምላክን የደፈረ ቢሆንም እንኳ ፣ አንድን ሰው ነጻ ያደርጋል ብሎ የሊቀ ጳጳሳቱን የስርየት ጽሑፍ አልቆ ማየት እብደት ነው ።

76. እኛ ግን በተቃራኒው የሊቀ ጳጳሳቱ የስርየት ጽሑፍ በደልን በሚመለከት ይቅር ሊባል የሚችል ከሁሉ ያነሰ ኀጢአትን ሊያስወግድ አይችልም እንላለን ።

77. ቅዱስ ጴጥሮስ እንኳ አሁን ሊቀ ጳጳሳት ቢሆን ኖሮ የሚበልጥ ጸጋ መስጠት አይችልም ነበር ብሎ መናገር ቅዱስ ጴጥሮስንና ሊቀ ጳጳሳቱን መሳደብ ነው ።

78. እኛ ግን በተቃራኒው የአሁኑ ሊቀ ጳጳሳት እንኳ ቢሆን ወይም ሌላ ማንኛውም ሊቀ ጳጳሳት የሚበልጥ ጸጋ አለው ፣ ይኸውም



Scanned by CamScanner

በ1 ቆሮ. 12፥28 እንደ ተጻፈው ወንጌል ፥ መን ፈሳዊ ኃይል ፥ የፈውስ ስጦታ ፥ የመሳሰለውም አለው እንላለን ።

79. በሊቀ ጳጳሳቱ ካባ ላይ የተጌጠውና በስርየት ወረቀት ሰባክያን የተተከለው መስቀል ከክር ስቶስ መስቀል ጋር የሚተካከል ዋጋ አለው ብሎ መናገር ስድብ ነው ።

80. እንዲህ ያለው ወሬ በሕዝቡ ሙሐል እንዲነዛ የሚፈቅዱ ጳጳሳት ፥ ቀሳውስት ፥ እንዲሁም የሥነ መለኮት ሰዎች ይህን በሚመለከት ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል ።

81. ይህ ልቅ የሆነ የስርየት ጽሑፍ ስብከት ለሊቀ ጳጳሳቱ የሚገባውን አክብሮት ከሐሜት ወይም ከተራ ምእመናን የተንኰል ጥያቄ ለመጠበቅ ለተማሩ ሰዎች እንኳ አስቸጋሪ ያደርገዋል ።

82. ጥያቄውም የሚከተለውን ይመስላል ፡- «ሊቀ ጳጳሳቱ ለቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ የሚሆን ፋይዳ ቢስ ገንዘብ ሲል ቍጥራቸው ከ እስከ የማይባል ነፍሳትን የሚያድን ከሆነ ስለ ተቀ ደሰ ፍቅርና እዚያ ሊላሉት ነፍሳት አንገብጋቢ ችግር ሲል ዓፀደ ንስሐን ለምን ባዶ አያደር ግም ?» የመጀመሪያው ምክንያት እጅግ በጣም ትክክል ሲሆን ፥ ሁለተኛው ግን ዋጋ ቢስ ነው።



Scanned by CamScanner

83. ከዚህም በላይ ፡ «የቀብርና የሙታን መታሰቢያ ቅዳሴ መካሄድ የሚቀጥለው ለምንድር ነው ? ለዳኑት መጸለይ ኀሕተት በመሆኑ ለሙታን የተመደበውን ስጦታ ሊቀ ጳጳሳቱ ለምን አይ መልስም ወይም እንዲነሣ አይፈቅድም ?»

84. በተጨማሪ ፡ «እግዚአብሔርና ሊቀ ጳጳሳቱ ለገንዘብ ሲሉ ታማኝ ያልሆነና ጠላታቸው የሆነ ሰው የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነውን ሰው ታማኝ ነፍስ ከዓፀደ ንስሐ ገዝቶ ለማውጣት የሚፈቅዱበት ይህ አዲስ መታመን ምንድር ነው ? ይልቁንስ በዚያ ታማኝና ውድ ነፍስ ፍላጎት ምክንያት ስለ ንጹሕ ፍቅር ሲሉ ነጻ አይለቁትምን ?»

85. ከዚህም በላይ ፡ «ከተሻረና ያለ አግባብ በሆነ አጠቃቀም ምክንያት ከቀረ ረጅም ጊዜ የሆነው ንስሐን የሚመለከተው ቀኖና በስርየት ጽሑፍ መሰጠት አሁንም እንዳለና እንደሚሠራ ሆኖ ለምን ይታያል ?»

86. በተጨማሪ «በአሁኑ ጊዜ ሀብቱ ከሁሉ በላይ ከሆነው ሰው ሀብት የሚበልጠው ሊቀ ጳጳሳት ይህንን የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ድሆች በሆኑ አማኞች ገንዘብ ከመሥራት ይልቅ ፡ በራሱ ገንዘብ የማይሠራው ለምንድን ነው ?»



Scanned by CamScanner

87. ከዚህም በላይ ፣ «ፍጹም በሆነ ጸጸት ቀድሞ ውኑ ሙሉ የሆነ የኃጢአት ይቅርታና በረከት የማግኘት መብት ላላቸው ሰዎች ሊቀ ጳጳሳቱ ምን ይሰጣቸዋል ?»

88. በተጨማሪ «ሊቀ ጳጳሳቱ አሁን በስርየት ወረቀት አማካይነት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚያደርገው ሳይሆን ይህንን የኃጢአት ይቅርታና በረከት ለእያንዳንዱ አማኝ በቀን መቶ ጊዜ የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ያህል በረከት ሊወርድ ይችል ነበር ?

89. «ሊቀ ጳጳሳቱ በስርየት ጽሑፍ ከሚያገኘው ገንዘብ ይልቅ የነፍሳትን መዳን የሚሻ በመሆኑ እኩል ብቃት ያለውን አስቀድሞ የተሰጠውን የስርየት ጽሑፍና ይቅርታ ለምን ያግዳል ?»

90. ይህንን እጅግ ጠንከር ያለ የተራ ሰዎች ክርክር ማስረጃ በመስጠት አለመፍታት ፣ በኃይል ብቻ መግታት ቤተ ክርስቲያንንና ሊቀ ጳጳሳቱን ለጠላቶቻቸው መሳለቂያ ማድረግ ፣ እንዲሁም ክርስቲያኖችን ማሳዘን ነው ።

91. ስለዚህ የስርየት ጽሑፍ በሊቀ ጳጳሳቱ ስሜትና አሳብ መሠረት የሚሰበክ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ጥርጥር ያለ ምንም ማመንታት መፍትሔ ያገኝ ነበር ። ጥርጥርም በእርግጥ አይኖርም ነበር ።



Scanned by CamScanner

92. እንግዲያውስ ለክርስቶስ ሕዝብ ሰላም ሳይሆን፥ «ሰላም ፥ ሰላም» (ኤር. 6፥14) የሚሉ ነቢያት ፥ ሁሉ ይወገዱ ።

93. ለክርስቶስ ሕዝብ መስቀል ሳይሆን ፥ «መስቀል ፥ መስቀል» የሚሉ ነቢያት ሁሉ የተባረኩ ይሁኑ ።

94. ክርስቲያኖች ሁሉ ራሳቸው የሆነውን ክርስቶስን በቅጣት ፥ በሞት እንዲሁም በሲኦል በጥብቅ እንዲከተሉት ማደፋፈር ይገባል ።

95. ስለዚህ ውሸት ሆን የሰላም ዋስትና ሳይሆን ፥ በብዙ መከራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት እምነት ሊኖራቸው ይገባል ።

## ም ን ጭ


1. Harold G. Grimm(ed): The Ninety-Five Theses or the Disputation Concerning the value of Indulgences: Luther's Works, Fortress Press Vol. 31. USA 1957.

2. Cover Picture: Adopted from Compton's Pictured Encyclopedia and Fact Index Compton and Company Vol. 12 USA 1963




Scanned by CamScanner